መልእክት ሁለት

## ለሕይወታዊ መጨመሯ የቤተ ክርስቲያን ውስጠ-መሠረታዊ እድገት

የመጽሐፍ-ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ቆላ. 2፡19፤ ኤፌ. 4፡13፣ 15-16፤ 1 ቆሮ. 3፡6-7፤ 12፡12፤ ዮሐ. 3፡29-30፣ 34

1. **የቤተ ክርስቲያን ውስጠ መሠረታዊ እድገት፣ ሕይወታዊው እድገት በመለኮታዊው ሕይወት፣ ይህም በሂደት ባለፈው እና በሚያድለው ሦስታንዱ አምላክ የሆነ እድገት ነው—ኤፌ. 4፡15-16፤ 3፡16-17፤ 2 ቆሮ. 13፡14፡-**

ሀ. ቤተ ክርስቲያን የምታድገው በዚህ ሕይወት ውስጥ፣ በዚህ ሕይወት፣ ከዚህ ሕይወት ጋር እና በዚህ ሕይወት በኩል ነው፤ ከመለኮታዊው ሕይወት፣ ከእግዚአብሔር ከራሱ ተወልደናል፣ እግዚአብሔርም አሁን እንድናድግ እያደረገን ነው—ዮሐ. 1፡12-13፤ 1 ቆሮ. 3፡6።

ለ. ቆላስይስ 2፡19 ስለ አካሉ እድገት ይናገራል፣ ይህም በውስጣችን የእግዚአብሔር ማደግ ነው፡-

1. ማደግ ክርስቶስ ወደ ውስጣችን መጨመሩ ነው—1 ቆሮ. 3፡6-7፤ ገላ. 4፡19።
2. የአካሉ እድገት የሚመረኮዘው ራስ ከሆነው ክርስቶስ በሚወጣው ነገር ላይ ነው—ኤፌ. 4፡15-16።
   ሀ. አካሉ [የአካሉን] ራስ በመያዝ አቅርቦት ሲያገኝ፣ አካሉ በእግዚአብሔር ማደግ ያድጋል—ቆላ. 2፡19።
   ለ. አካሉ [ከአካሉ] ራስ የተነሣ ያድጋል፣ ምክንያቱም አቅርቦቱ ሁሉ የሚመጣው [ከአካሉ] ራስ ነውና—ኤፌ. 4፡15-16።
3. የአካሉ እድገት የሚመረኮዘው በውስጣችን ባለው በእግዚአብሔር ማደግ፣ በእግዚአብሔር መደመር፣ በእግዚአብሔር መጨመር ላይ ነው—ቆላ. 2፡19፡-
   ሀ. እግዚአብሔር በራሱ የሚያድግ አይደለም፣ ምክንያቱም እርሱ ሙሉ እና ፍጹም ነው፤ እርሱ የሚያድገው በውስጣችን ነው።
   ለ. እግዚአብሔር እድገትን የሚሰጠው ራሱን ለእኛ ውስጠ-ልምምዳዊ በሆነ መንገድ በመስጠት ነው።
   ሐ. እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን አብዝቶ ሲጨመር፣ ብዙ እድገትን ይሰጠናል፤ እግዚአብሔር እድገትን የሚሰጥበት መንገድ ይህ ነው—1 ቆሮ. 3፡6-7።
   መ. እግዚአብሔር ብቻ እድገትን መስጠት ይችላል፤ እግዚአብሔር ብቻ ራሱን ሊሰጠን ይችላል፣ ያለ እርሱ እድገት ሊኖረን አይችልም—ቁ. 6-7።
      (1) የእግዚአብሔር ወደ ውስጣችን መጨመር እርሱ የሚሰጠው እድገት ነው።
      (2) እግዚአብሔር ለእኛ እድገት መስጠቱ ማለት ራሱን ይሰጠናል ማለት ነው—ሮሜ 8፡11።
      (3) እግዚአብሔር የሕይወት እድገት ለእኛ መስጠቱ ማለት ራሱን በውስጣችን እየጨመረ ነው ማለት ነው።
4. እግዚአብሔር በውስጣችን የሚያድግበት መጠን የሚመረኮዘው ያድግ ዘንድ ለእርሱ በምንሰጠው ክፍል መጠን ላይ ነው—ኤፌ. 3፡17፤ ቆላ. 3፡16፡-
   ሀ. በውስጣችን ለእግዚአብሔር ክፍል ስንሰጠው፣ በውስጣችን ይስፋፋል ይጨምርማል፤ ይህ መጨመር እርሱ በውስጣችን ማደጉ ነው።
   ለ. የእግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ማደግ የእኛ ማደግ ይሆናል ምክንያቱም እርሱ እና እኛ አንድ ነን—1 ቆሮ. 6፡17።
5. የክርስቶስ አካል የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ማደግ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔር ማደግ ነው—ቆላ. 2፡19።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን ወደ ብስለት—"የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ"—እስክትደርስ ድረስ ታድጋለች—ኤፌ. 4፡13፡-

1. ክርስቶስ ሙላት አለው፣ ሙላቱ ቁመተ-አቋም አለው፣ ቁመተ-አቋሙ ደግሞ ልክ አለው።
2. የክርስቶስ አካል የእርሱ ሙላት፣ የእርሱ መገለጥ ናት—1፡23፡-
   ሀ. ያለምንም ገደብ የማይወሰን አምላክ የሆነው ክርስቶስ እጅግ ታላቅ ነው፣ ሁሉን ነገሮች በሁሉ ነገሮች ይሞላልና።
   ለ. እንዲህ ያለው ታላቅ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሙሉ ለሆነ መገለጡ የእርሱ ሙላት ትሆን ዘንድ ታስፈልገዋለች—ቁ. 22-23።
   ሐ. የክርስቶስን ብልጥግናዎች በመደሰት በኩል (3፡8)፣ ሙሉ ለሆነ መገለጡ የእርሱ ሙላት እንሆናለን።
3. አካሉ የሆነችው የክርስቶስ ሙላት ቁመተ-አቋም አላት፤ የክርስቶስ ሙላት ቁመተ-አቋም የክርስቶስ አካል ቁመተ-አቋም ነው—4፡13፤ 1፡23።
4. የክርስቶስ ሙላት ቁመተ-አቋም አላት፣ ይህም ቁመተ-አቋም ልክ አለው—4፡13፡-

ሀ. የቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ አካል ቁመተ-አቋም የሚያድግ ስለሆነ፣ ጳውሎስ ስለ ልኩ ይናገራል፤ ይህ ልክ ሙሉ በሙሉ-ያደገ ሰው ነው—ቁ. 13፦

ለ. ሙሉ በሙሉ- ያደገ ሰው ወደ መሆን፣ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እየመጣን ነው፦

(1) የክርስቶስም ሙላቱ የሚሆን የሙላቱ ልክ ያለው መሆን የተናጠል ግለሰቦች ጉዳይ አይደለም፤ ይህ ብዙዎች-የተካተቱበት አካል ጉዳይ ነው።

(2) ክርስቶስ በውስጣችን ሲያድግ ሳለ፣ እኛ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ ቀስ በቀስ እንደርሳለን።

(3) እኛ ሁላችን የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ መገስገስ ያስፈልገናል፤ ይህ ግባችን ነው፣ እኛ ሁላችን በአንድ ላይ እስከንደርሰበት ድረስ በትጋት ወደ እዚያ መገስገስ አለብን—ፊልጵ. 3፡12-14።

## II. የቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ መጨመር እንደ ሙሽራው በሕይወታዊ አካሉ ውስጥ ያለ የክርስቶስ መጨመር ነው—ዮሐ. 3፡29-30፦

ሀ. የክርስቶስ ሙላት አካሉ ናት፣ አካሉ አምሳያው፣ ሙሽራው ናት—ኤፌ. 4፡12-13፣ 16፤ 5፡25-27።

ለ. "ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው...። እርሱ ሊልቅ ያስፈልጋል"—ዮሐ. 3፡29-30፦

1. በዮሐንስ 3፡30 ያለው መጨመር (መላቅ) በቁጥር 29 ያለችው ሙሽራይቱ ናት፣ ሙሽራይቱ ዳግም ከተወለዱ ሰዎች ሁሉ የተዋቀረች ናት።
2. ዳግም መወለድ መለኮታዊውን ሕይወት ወደ አማኞች ውስጥ የሚያመጣ ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስ መጨመር ብዙዎች የተካተቱባት ሙሽራ የሚያደርጋቸውም ጭምር ነው—ቁ. 3፣ 5-6፣ 29-30።
3. ክርስቶስ የሚጨምረው የተዋጁ ኃጢአተኞችን ዳግም በመውለድ፣ ሙሽራው በማድረግ ነው—ቁ. 29።

ሐ. የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ሦስት የሚጨምረውን ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርን ቃሎች የሚናገረውን እና መንፈስን ሰፍሮ የማይሰጠውን እርሱን ይገልጣል—ቁ. 34፦

1. አንድ ሰው ቃሎቹን ሲቀበል፣ መንፈስ የተነገረው [ቃል] እውነታ ለመሆን ይከተላል።
2. ክርስቶስ ራሱን የሚጨምረው እግዚአብሔርን ለማሰራጨት የእግዚአብሔርን ቃል በመናገር እና የተናገረው ነገር እውነታ እንዲሆን የእግዚአብሔርን መንፈስ በመስጠት ነው፣ ይህም የክርስቶስ መጨመር እንዲሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ለማድረግ ዘላለማዊውን ሕይወት ወደ ሰዎች ውስጥ ለማደል ነው፤ ክርስቶስ የሚጨምረው ክርስቶስ (the increasing Christ) የሚሆነው እንደዚህ ነው—6፡63፤ 3፡30፣ 34።

መ. የክርስቶስ መጨመር የክርስቶስ ብዜት እና ርቢ ነው፤ ዳግም የተወለደው የማንነታችን ክፍል የክርስቶስ መጨመር፣ የሙሽራይቱ ክፍል ነው—ቁ. 6።

ሠ. ሙሽራይቱ እንደ የክርስቶስ መጨመር ክርስቶስ ራሱ ናት ምክንያቱም የክርስቶስ አካል—"ክርስቶስ" (1 ቆሮ. 12፡12)—ብዙዎች የተካተቱበት ክርስቶስ ነው፣ ይህም ራስ ከሆነው ክርስቶስ እና አካሉ ከሆነችው ቤተ ክርስቲያን ብልቶች ከሆኑት አማኞች ሁሉ ጋር የተዋቀረ ነው።

© 2021 Living Stream Ministry